# ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣውን የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 76/2004

ሰኔ 2004 ዓ.ም

## ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣውን የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 76/2004

የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የጉምሩክ መጋዘን ኪራይ ማስከፈያ መጣኔ መጋዘኑን ለማስተዳደር የሚወጣውን አጠቃላይ ወጪ ሊሸፍን በሚያስችል አግባብ መሻሻል እንዳለበት በመታመኑ፤

አሁን ባለው ሁኔታ በአየር ተጓጉዘው ወደ ሀገር ለሚገቡና ከሀገር ለሚወጡ ዕቃዎች የመጋዘን ኪራይ ማስከፈያ መጣኔ ድርጅቶቹ የተለያዩ መጣኔ አውጥተው የሚያስከፍሉ ስለሆነ በድርጅቶቹ መካከል ወጥ የሆነ የመጋዘን ኪራይ ማስከፈያ መጣኔ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 30(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣውን የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 76/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

   1/ ከመመሪያው አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ (6) ቀጥሎ የሚከተለው ንዑስ አንቀፅ (7) ተጨምሯል

   7. **"የሚበላሹ እቃዎች"** ማለት በባህሪያቸው ምክንያት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከመፈፀሙ በፊት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞ እቃዎቹ ከመለቀቃቸው በፊት ከጥቅም ውጪ ሊሆኑ የሚችሉ እና ለማቆየት የተለየ አያያዝ የሚያስፈልጋቸው እቃዎች ናቸው፡፡

   2/ የመመሪያው አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ (7)፤ (8) እና (9) እንደቀደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀፅ (8)፤(9) እና (10) ሆነዋል፡፡

3/ የመመሪያው አንቀፅ 13 ተሰርዞ እንደሚከተለው ተሸሽሏል፡፡

13. **<u>የኪራይ ተመን</u>**

በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ የገባ ማንኛውም እቃ በመጋዘን ውስጥ ለቆየባቸው ለእያንዳንዱ ቀን ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት የመጋዘን ኪራይ ይከፈልበታል፡፡

1. በየብስ ተጓጉዘው ወደ መጋዘን ለሚገቡ ዕቃዎች

ሀ/ በዝግና እና ክፍት መጋዘን ለሚራገፉ፡-

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ/በቀናት | ተመን/በኪሎ ግራም በብር |
|---|---|---|
| 1 | 1-10 | 0.0075 |
| 2 | 11- 20 | 0.01 |
| 3 | 21- 30 | 0.015 |
| 4 | ከ30 ቀናት በላይ | 0.02 |
| 5 | በመልቲ ሞዳል ሥርዓት ተጓጉዞ ወደ ሀገር ለገባ ዕቃ ከ1-3 ቀናት | ነፃ |

- ለመድን ዋስትና ሽፋን(Insurance) 0.06 ከብር 1000፣ CIF
- ለመሳሪያዎች አገልግሎት(ለመጫንና ለማውረድ) ብር 250፣ እስከ 20 ቶን
  ብር 350፣ ከ20-30 ቶን
  ብር 400፣ ከ30 ቶን በላይ

ለ/ በተሽከርካሪ ላይ እንደተጫነ ለሚፈተሹ፡-

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ/በቀናት | ተመን/በኪሎ ግራም በብር |
|---|---|---|
| 1 | 1-10 | 0.01 |
| 2 | 11- 20 | 0.015 |
| 3 | 21- 30 | 0.02 |
| 4 | ከ30 ቀናት በላይ | 0.025 |

- ለመድን ዋስትና ሽፋን (Insurance) 0.06 ከብር 1000፣ CIF

2. በአየር ተንጉዞ ወደ መጋዘን ለገባ የመንገደኞች ዕቃ

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ (በቀናት) | ተመን/በኪሎ ግራም በብር |
|---|---|---|
| 1 | 1 | ነፃ |
| 2 | 2-10 | 2.00 |
| 3 | ከ11 ቀናት በላይ | 2.40 |

3. ሀ/ በአየር ተንጉዞ ለገባ ዕቃ

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ (በቀናት) | ከ1000 ኪ.ግ በታች ተመን/ በኪሎ ግራም በብር/ | ከ1000 ኪ.ግ በላይ ተመን/ በኪሎ ግራም በብር/ |
|---|---|---|---|
| 1 | 1-3 | ነፃ | ነፃ |
| 2 | 4-10 | 0.05 | 0.15 |
| 3 | 11-30 | 0.10 | 0.2 |
| 4 | ከ30 ቀናት በላይ | 0.2 | 0.3 |

ለ/ በአየር ተንጉዞ ወደ ሀገር ውስጥ ለገባ የሚበላሽ ዕቃ

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ (በቀናት) | ተመን/ በኪሎ ግራም በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | 1-10 | 0.80 |
| 2 | ከ10 ቀናት በላይ | 1.00 |

ሐ/ በአየር ተንጉዞ ከሀገር ለሚወጣ የሚበላሽ ዕቃ

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ (በቀናት) | ከ1000 ኪ.ግ በታች ተመን/ በኪሎ ግራም በብር/ | ከ1001-2000 ኪ.ግ ተመን/ በኪሎ ግራም በብር/ | ከ2000 ኪ.ግ በላይ ተመን/ በኪሎ ግራም በብር/ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 1-2 | 0.30 | 0.25 | 0.20 |
| 2 | 2-90 | 0.45 | 0.35 | 0.25 |

4. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል ከ1 (አንድ) ኪሎ ግራም በታች የሚመዝን እቃ እንደ አንድ ኪሎ ግራም ተደርጐ ይወስዳል፡፡

5. <u>**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**</u>

ይህ መመሪያ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች አፈፃፀም በነበረው መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

6. <u>**መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ _______ ቀን 2004 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር